# ሆዱን ያየ ሆዱን ተወጋ

*ይህ፡ ግጥም፡ለሆዳቸው፡ ሲሉ፡ ህሊናቸውን፡በቆራጥነት፡ ለገበሩ*
*ወንድምና፡ እህቶች፡ መታሰቢያ፡ ይሁን።*

ህዳሴ፡ህዳሴ፡ ብሎ፡ ለፈለፈ፡

ምድረ ሆዳም ሁሉ አሰፈሰፈ

ፍርፋሪ አገኝ ብሎ አነፈነፈ

ከዘረኞች ጋራ ባንዴ ተሰለፈ።

ስማ ሆዳሜ የአገር ሸክም፡

ያገኘህ መስሎህ ጥቅማ ጥቅም

አትሯሯጥ አትቀላውጥ

ሀገር ህዝብህን አትሽጥ።

ህዳሴ ህዳሴ ብለው ሲነግሩህ

በደደቢት ቋንቋ ሲያጭበረብሩህ

አንተም አመነሃቸው እውነት መስሎህ

ተከትለህ ስትሮጥ ትንፋሽ እስኪያጥርህ

ትንሽ ባገኝ ብለህ ከሚዘረፈው

የህዝቡን መበደል ከደህ አረፍከው።

ታሪክህ ሲነገር ይኸ ዘመን አልፎ

የከህደትህ መጠን አያልቅም ተጽፎ።

ተው ተመለስ እባክህ ጊዜው ሳይረፍድ ብዙ

ለሆድ ብሎ ማደር ትልቅ ነው መዘዙ

ለትውልድ ይተርፋል ሸክሙና ጓዙ።

ታዛቢ